የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 31
ADDIS ABABA - 5th March, 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፯/፲፱፻፺ ዓ.ም.
የኢትዮጵያና የጣሊያን የባህል ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...... ገጽ ፯፻፳፬

## CONTENTS

Proclamation No.107/1998
Ethio-Italian Cultural Cooperation Agreement Ratification Proclamation ...... Page 724

### አዋጅ ቁጥር ፻፯/፲፱፻፺

### የኢትዮጵያና የጣሊያን የባህል ትብብር ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ኤፕሪል ፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ሮም ላይ የባህል ትብብር ስምምነት የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው ተዋዋዮቹ ሀገሮች በየሕገመንግሥታቸው ሥርዓት መሠረት አስፈላጊውን በማሟላት ስምምነቱን ካጸደቁና የማረጋገጫውን ሰነድ ልውውጥ አዲስ አበባ ላይ ካደረጉ ከስድሳ ቀን በኋላ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፤

ይህንኑ የትብብር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያና የጣሊያን የባህል ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፻፯/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል እ.ኤ. አ. ኤፕሪል ፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ሮም ላይ የተፈረመው የባህል ትብብር ስምምነት ጸድቋል።

### PROCLAMATION NO. 107/1998

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO-ITALIAN AGREEMENT ON CULTURAL COOPERATION

WHEREAS, the Agreement on Cutlural Cooperation betweeen the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Italy was signed in Rome on the 8th day of April, 1997;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come into force sixty days from the exchange, in Addis Ababa, of instruments of ratification effected in compliance with the respective constitutional formalities of the Contracting Parties;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at it session held on the 5th day of March, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Ethio-Italian Cultural Cooperation Agreement Ratification Proclamation No. 107/1998."

2. *Ratification of the Agreement*

   The Agreement on Cultural Cooperation between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Italy signed in Rome on the 8th day of April, 1997 is hereby ratified.

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· <u>የሚመለከታቸው የፌዴራል አካላት ሥልጣን</u>

የትምህርት ሚኒስቴር፣ የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር፣ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የስፖርት ኮሚሽንና በስምምነቱ የተካተቱ የትብብር መስኮች የሚመለከታቸው ሌሎች ፌዴራል አካላት በየሥራ መስካቸው ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቷቸዋል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3. *Power of Concerned Federal Organs*

The Ministry of Education, the Ministry of Information and Culture, the Ministry of Labour and Social Affairs, the Sports Commission and other federal organs concerned with the fields of cooperation included in the Agreement are hereby empowered to implement the Agreement with regard to their respective fields of activity.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 5th day of March, 1998.

Done at Addis Ababa, this 5th day of March, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE